በብልጽግና ፓርቲ የአማራ ክልል የቁጥጥርና ኢንስፔክሽን ኮሚሽን የስራ አፈጻጸም እና ምክረ ሃሳቦች የያዘ ለመሰረታዊ ድርጅት የሚቀርብ ሰነድ!

የካቲት 2014 ዓ/ም

ባህር ዳር

1. መግቢያ

የአማራ ብልጽግና ቁጥጥርና ኢንስፔክሽን ኮሚሽን በብልጽግና ፓርቲ መተዳደሪ ደንብ አንቀጽ 23 ንኡስ አንቀጽ 6 ከተራ ቁጥር "ሀ" እስከ "ቸ" ድርስ የተቀመጡ ዝርዝር ተግባርና ሀላፊነት ተሰጥቶታል። በመተዳደሪያ ደንቡ በተሰጠው መሰረት

ባለፉት ሶስት አመታት ከክልል እስከ መሰረታዊ ድርጅት ድረስ ተግባራትን ሲያከናውን ቆይቷል። የውስጠ ፓርቲ ዲሞክራሲና ሌሎች የፓርቲውን ችግሮች በፓርቲው ህገደንብ መሰረት ለመፍታትና ለፓርቲው አጋዥ ይሆን ዘንድ ርብርብ ማድረግ እና መሰል አቅጣጫዎችን ለመተግበር ጥረቶች ሲደረግ ቆይቷል።

በዚሁ መሰረት የፓርቲው ቁጥጥርና ኢንስፔክሽን ኮሚሽን አደረጃጀትና አሰራሩን ያለበት ሁኔታ፣ የኮሚሽኑ የእቅድ አፈፃፀም፣ የፓርቲው የሀብትና የንብረት እንደዚሁም የሰነድና የመረጃ አያያዝን በተመለከተ፣ በየደረጃው የሚገኙ የፓርቲ አባላት መብቶች መከበራቸውን የማረጋገጥ፣ የኮሚሽኑ አጠቃላይ የድጋፍና የክትትል ሁኔታ፣ ያጋጠሙ ችግሮችንና እንዲሁም የቀጣይ የትኩረት አቅጣጫዎችን የሚያሳይ በአጭር በአጭሩ ሪፖርት እንደሚከተለው በዚህ ሰነድ ተካቶ ቀርቧል።

2. ኮሚሽኑን ከማጠናከር አንጻር በፓርቲው በኩል የነበሩ ጥንካሬዎች

የብልጽግና ፓርቲ ማእከላዊ ቁጥጥርና ኢንስፔክሽን ኮሚሽን በፓርቲያችን ጠቅላላ ጉባኤ የተመረጠ የፓርቲው ከፍተኛ የአመራር አካል ነው። በብልጽግና ፓርቲ መተዳደሪያ ደንብ አንቀጽ 23 ንኡስ አንቀጽ 1፣3፣4 እና 5 ላይ ተገልጻል የቁጥጥርና ኢንስፔክስን ኮሚሽን ከፓርቲው ጉባኤ በሚመረጡ አባላት ይዋቀራል ብሎ አስቀምጧል። በዚህም መሰረት የፓርቲውን ፕሮግራም፣ መተዳደሪያ-ደንብና አሰራሮች በአግባቡ ሥራ ላይ መዋላቸዉን የመከታተል፣ በአጠቃላይም የፓርቲዉ የውስጠ ፓርቲ ዴሞክራሲ እንዲጠናከር የማድረግ ሚናው ከፍተኛ ነው። ከዚህ አንጻር ሲታይ የብልጽግና ፓርቲ እንደ ተቋም የፓርቲው አንዱ ትልቅ አካል የሆነውን የቁጥጥርና ኢንስፔክሽን ኮሚሽን በህገ-ደንቡ ላይ እስከ ዛሬ ያልነበረዉን ሃላፊነት ጭምር እንዲካተት በማድረግ የወሰደዉ ፖለቲካዊ የለውጥና ሪፎርም እርምጃ በኮሚሽኑ ታሪክ ትልቅ ቦታ የሚሰጠዉ ጉዳይ ነዉ። ከዚህ በተጨማሪ አሁን በስራ ላይ ያለዉ የፓርቲዉ መተዳደሪያ ደንብ በምክር ቤቱ ሲጸድቅ የፓርቲዉ ከፍተኛ አመራር ባስቀመጠዉ አቅጣጫ መሰረት ለፓርቲዉ የዉስጥ ዲሞክራሲ መጎልበት መሰረታዊ የሆኑና ኮሚሽኑ በጥናት ላይ ተመስርቶ ለፓርቲዉ ያቀረባቸዉ ነጥቦች አብዛኞቹ በረቂቅ መተዳደሪያ-ደንቡ ላይ እንዲካተቱ ተደርጓል። ይህም ኮሚሽኑን የበለጠ ጠንካራ፣ እውነተኛ አቅም ያለውና ነጻ የፓርቲ ተቋም ሆኖ በፓርቲዉ የለዉጥና የብልጽግና ጉዞ ትልቅ ሚና እንዲጫወት የሚያደርግ የፖለቲካ እርምጃ ነዉ።

በብልጽግና ፓርቲ መተዳደሪያ ደንብ አንቀጽ 12 ንኡስ አንቀጽ 2 ተራ ቁጥር “ረ” ፓርቲው ከሚኖሩት ተቋማዊ መዋቅሮች አንዱ የቁጥጥርና ኢንስቴክሽን ኮሚሽን እንደሆነ አስቀምጧል። በዚህም መሰረት ከክልል አስከ ወረዳ ድረስ የኮሚሽኑን አደረጃጀት በሰው ሀይልና በቁሳቁስ ከማጠናከርና ከመደገፍ አንፃር አፈጻጸሙ ከዞን ዞንና ከወረዳ ወረዳ የተለያየ ቢሆንም በአመዛኙ ተግባራዊ ተደርጓል።

ኮሚሽኑ ከፓርቲው ጋር የነበረው በጋራ እየተገናኙ የመወያየት ጉዳይ በክልል ደረጃ፤ በዞንና በወረዳ የሚገኘው የኮሚሽን መዋቅር በተሟላ ደረጃም ባይሆን የተሻለ የግንኙነትና የምክክር ጊዜ ነበረን። በአጠቃላይ ሲታይ ከነክፍተቱም ቢሆን ኮሚሽኑን በየደረጃዉ ለማደራጀት፣ ለማጠናከርና ለመደገፍ በፓርቲዉ አሰፈጻሚ አካላት የተከናወኑት ተግባሮች ከነውስንነታቸውም ቢሆን በኮሚሽኑ ታሪክ ረጅም ርቀት ያራመዱና ለፓርቲዉ መጎልበትም አቅም የሚሆኑ የፓርቲያችን የለውጥና የሪፎርም ትሩፋቶች

ናቸዉ። የክልላችን የኮሚሽን መዋቅር ነፍስ ያለው ሆኖ እንዲደራጅ የብልጽግና ፓርቲ ምክትል ፕሬዝዳንት የኮሚሽኑ ከፍተኛ አመራሮች ያደረጉት ጉልህ አስተዋጽኦ እጅግ የሚመሰገን ነበር።

3. በፓርቲው ዘንድ የሚስተዋሉ ዋና ዋና ጉድለቶች

3.1. በጤናማ የፖለቲካ እሳቤ አባላትን መሳብና ማሰባሰብ የሚቻለው ጠንካራ፣ እምነትና ተስፋ የሚጣልበት የፓርቲ ፕሮግራምና መተዳደሪያ ደንብ ሲኖር እንደሆነ ሳይታለም የተፈታ ሃቅ ነው።

አዳዲስ አባላትን ለመሳብም ሆነ ያሉትን አቅቦ ማቆየት የሚቻለው እነዚህ ቁልፍ የሃሳብና የተግባር አንድነት መፍጠሪያ የፖለቲካ ሰነዶች ሲኖሩ፣ በተግባርም ሳይሸራረፉ፣ ከአደሎ የፀዱና አሳታፊ ሆነዉ ሲፈጸሙ ብቻ ነው። በዚህ ረገድ ብልጽግና አይታማም ብቻ ሳይሆን ከምንጊዜውም የተሻለ አካታችና ገቢራዊ (Pragmatic) ፕሮግራምና ህገ-ደንብ አዘጋጅቶ ወደ ስራ ገብቷል። ነገር ግን እነዚህ የትግል ሰነዶች የተሻሉ መሆናቸውና መኖራቸው ብቻ ሳይሆን ዋነኛ የፓርቲው መርህና የስራ መመሪያ ብሎም የተቋም መገንቢያ መሳሪያ ሆነው በጥብቅ ዲስፕሊን ሲተገበሩና አባላትም በአተገባበራቸዉ ላይ ጠንካራ እምነትና ጽናት ሲኖራቸው ብቻ ነዉ ብቁና ዉጤታማ ናቸዉ ሊባሉ የሚችሉት።

3.2. መቸም ይሁን የትም የአመራር ስምሪት (ሹም ሽር) የፓርቲ መተዳደሪያ-ደንብንና አሰራርን ተከትሎ ነጻ፣ ግልጽና አሳታፊ ሆኖ ቢፈጸም ትክክልና ወደፊትም የማይቀር እዉነታ ነዉ።

ሆኖም የፓርቲያችን የአመራርና የአባላት ስምሪት በብዙ አካባቢዎችና በየደረጃዉ በሚገኙ የፓርቲ አካላት ዘንድ አሳታፊነትና ግልፅነት የጎደለዉ፣ በፓርቲው መተዳደሪያ ደንብ፣ አሰራርና መርህ መሰረት የማይከወን፣ በኔትዎርክ በትዉዉቅ የሚፈጸም እየሆነ መጥቷል። ይህ አይነቱ የፓርቲ የህግ ጥሰት በፓርቲዉ አባላትና አመራሮች ዘንድ በየጊዜዉ ሰፊ ቅሬታና አቤቱታዎች እንዲቀርቡ እያደረገ ይገኛል። በርግጥ ተጨባጭ ጥፋቶች በተግባርም ይሁን በአመለካከት እየተገኘባቸዉ ከያዙት ሃላፊነት እንዲነሱ የተደረጉ ብዙ አባላትና አመራሮች አሉ ብቻ ሳይሆን፣ ይገምገሙም አይገምገሙም በችግራቸዉ ምክንያት ከሃላፊነት ሲባረሩ ወይም ሲነሱ ወዲያዉ እንደ እስስት ራሳቸዉን ቀይረዉ የፓርቲ ተጻራሪ በመሆን ያለና የሌለን ሁኔታ በየቦታዉና በየማህበራዊ ሚዲያዉ የሚያዘምሩና የሚያንጫጩ ብዙ ናቸዉ። በተቃራኒዉ የሚያሞግሳቸውንና አቤት ወዴት የሚላቸውን፣ “ለምን ሳይል ዝለል ሲባል ስንት ሜትር ልዝለል” የሚልን አድርባይ አመራር፣ አባልና አባል ያለሆነን ሰዉ እንጂ ችግርን የሚጠቁሙና በምክንያትና በሃሳብ የሚሞግታቸውን አባል የማይመድቡና ካለበት ሃላፊነት አንስተዉ በሌላ የሚተኩ የፓርቲዉ የአመራር አካላት (አስተባባሪዎች) ቁጥር በየአካባቢዉ እየተበራከተ መጥቷል። በአንዳንድ የአስተዳደር እርከኖች በየጊዜው እንደ አዲስ የሚሰየሙ አመራሮች በመጡ ቁጥር አምሳያቸውንና የሚመቻቸዉን አመራር ወይም አባል ወደ ስልጣን ለመሳብ ሲሉ ምንም አይነት የስራ አፈጻጸም ግምገማም ሆነ አባላትን ባሳተፈ ሁኔታ ሂስና ግለ ሂስ ሳያካሂዱ ቀኝ ሲባል ግራ የሚልና በተግባሩም ሆነ በአመለካከቱ ያረጠ አመራር እያለ ነባር ነዉ በሚል ሽፋን በሁሉም ሁኔታ ቢመዘን ጥሩ ደረጃ ላይ ያለን አመራር ከፓርቲ አሰራርና መርህ ውጪ እያነሱ በሚመቻቸዉን ሰዉ በመተካት በየጊዜው መዋቅሩን ሲቀያይሩት ይታያል። ስለሆነም ፓርቲ ሩቅ አስቦ ቅርብ እንዳያድር ከተፈለገ የተጠያቂነት መርህን የሚያሰፍን፣ በፓርቲ ህግና በጠንካራ ዲሲፒሊን

የሚተገበር፣ በገለልተኛና ነጻ የፓርቲ አካል ቁጥጥርና ኢንስፔክሽን የሚታገዝ የአመራር ስምሪት መመሪያና አተገባበር ሊኖርና እስካሁን ያጠፉትም ተገምግመዉ ትምህርት ሊወሰደበት ይገባል እንላለን።

3.3. የአንድ ፓርቲ የዉስጥ ጥንካሬ መገለጫዎች ከሆኑት ጉዳዮች አንዱ በየጊዜዉ ያለውን አደረጃጀትና አሰራር በመፈተሽ ያሉትን ጥንካሬዎች ለማሰቀጠልና እጥረቶችን ለማሰተከከል እንዲችል ተከታታይነት ያለዉ የአካል የስራ ግምገማ እና ሂስና ግለ-ሂስ በማካሄድ ፓርቲውንም ሆነ አባላትን ከውድቀትና ጥፋት መታደግ ነው።

የለዉጥ አመራርና አካላት በተጨባጭ ተግባር ዉጤት ሳያመጡ ያለፈዉን ችግር ብቻ ዘዉትር እየወቀሱና እየረገሙ አይኖሩም። በየጊዜዉ የአመራሩንና የአባላትን የተግባር፣ የአመለካከትና የስነ ምግባር ብቃት መለየትና የሚኖረዉን ወቅታዊ ክፍተት ለመሙላት በአቅም ግንባታ ስራና በዲስፕሊን እንዲታነጹ ማድረግ ይገባል። አሁን ባለዉ ተጨበጭ ሁኔታ ይህ ቁልፍ የዉስጠ ፓርቲ ጤናማ ዲሞክራሲያዊ ፖለቲካዊ ሂይወት መገንቢያ መሳሪያ እጅግ የተቀዛቀዘና ካለም ለሪፓርት ሲባል ለይስሙላ ብቻ ለብለብ ተደርጎ የሚካሄድ እየሆነ መጥቷል። ዴሞክራሲያዊ የዉይይትና የእዉነተኛ ግምገማ መድረኮች ሆን ተብለዉ በሚመስል ሁኔታ ተዳክመዋል። በዚህ ሳቢያም ተዉ ባይና ሞጋች እየጠፋ የፓርቲዉ መተዳደሪያ ደንብና አሰራሮች በየአካባቢዉ አካላትና አመራሮች በንቃትም ያለንቀትም እየተሸራረፉና እየተዘለሉ (Bypass) ስለሚፈጸሙ ሁኔታዉ ፓርቲያችንን ለብዙ የአባላትና የአመራር ቅሬታ፣ አሉባልታና ጥርጣሬ ሲዳርግ ይታያል። በዚህ ምክንያት የፓርቲው የሲስተም ስብራት ጎልቶ እየታየ ሁኔታዉንም የፓርቲ ጽ/ቤቶች በተሎ ማረምና ማስተካከል ካልቻሉ ጉዳዩ ፀረ-ዴሞክራሲያዊነት ሊያመራ የመቻል እድሉን ሰፊ ያደርገዋል፣

3.4. ከላይ ከተገለጸዉ ሃሳብ ጋር ተያያዥነት ባለዉ መልኩ መታየት ያለበትና ልዩ ትኩረት ሊሰጠው የሚገባዉ ጉዳይ የፓርቲዉ የአመራርና የአባላት አቅም ግንባታ ስራ ነው።

የአባላት አቅም ግንባታ ስራዎች በብልጽግና ፓርቲ መተዳደሪያ ደንብ አንቀጽ 23 ንኡስ እቀጽ 6 ከተራ ቁጥር "ሀ" እስከ "ቸ" የተሰጡትን ተግባርና ሀላፊነቶችን በብቃት ለመፈጸም የአቅም ግንባታ ስራዎች ያስፈልጋሉ።ፓርቲዉ ከሌሎች የዉስጠ ፓርቲ ስራዎች ጎን ለጎን በየጊዜዉ ወቅታዊና ነባራዊ ሁኔታዎችን መነሻ ያደረገ አዳዲስ ሀሰቦችን ማስረጽ የሚያስችሉ ጽሁፎችን፣ የመወያያ ሰነዶችን እና ልሳናቶችን በማዘጋጀት ለአባሉ ከማዉረድና ከማብቃት አንጻር ሰፊ ዉስንነቶች አሉበት። ብዙ አመራሮች አዳዲስ ሀሳቦችን የማፍለቅና የመተንተን ችግር አለባቸዉ። የፓርቲዉን ራዕይና ግብ ብሎም በፓርቲዉ የመደመር አስተሰሰብ ልዕልና ዙሪያ ለአባሉም ሆነ ለአመራሩ ተከታታይነት ያለዉ ግንዛቤ ከመፍጠር አንጻር ቀላል የማይባሉ ችግሮችም አሉባቸዉ። የፓርቲው ዝቅተኛ አደረጃጀቶች የሆኑት መ/ድርጅቶችና ህዋሳት ዋነኛ ፓርቲው የአባላት አቅም የሚገነባባቸው መድረኮች መሆናቸው እየታወቀ እነዚህን ዋነኛ የፓርቲው ተቋማዊ መሰረት የሆኑ አደረጃጀቶች በበርካታ ቦታዎች በቁጥርና በወረቀት ላይ እንጂ በተግባር አቅማቸዉ ተገንብቶ የማናገኛቸው ናቸዉ። ይህም ከሌሎች የዉስጠ ፓርቲ ችግሮቻችን ጋር ተደምሮ በፓርቲው ውስጥ የፓርቲ የሃሳብና የተግባር አንድነት እንዳይፈጠር፣ ጠንካራ የፓርቲ ዲስፕሊን እንዳይኖር እያደረገ ይገኛል።

4. የቁጥጥርና ኢንስፔክሽን ኮሚሽኑ ጥንካሬዎችና ጉድለቶች

4.1. ኮሚሽኑን የተመለከቱ ዋና ዋና ጥንካሬዎች

የቁጥጥርና ኢንስፔክሽን ኮሚሽን የፓርቲዉ ጠንካራ ክንድ ሆኖ መጓዝ የሚችለዉ ተቋማዊ አደረጃጀትና አሰራሩን በማሰተካከል ወደ ስራ መግባት ሲችል ነዉ። የኮሚሽኑ አደረጃጀት በብልጽግና ፓርቲ መተዳደሪያ ደንብ አንቀጽ 23 ንኡስ አንቀጽ 1፣3፣4 እና 5 ላይ ተገልጻል የቁጥጥርና ኢንስፔክሽን ኮሚሽን ከፓርቲው ጉባኤ በሚመረጡ አባላት ይዋቀራል ብሎ አስቀምጧል። በኮሚሽኑ መመሪያ መሰረት በክልል ደረጃ በቋሚነትም ሆነ በአማተርነት የሚሰሩትን ጨምሮ ከ 11-15 የኮሚሽን አመራሮች የሚሰየሙ ሲሆን ድጋፍ ሰጭዎችን ሳይጨምር የጽ/ቤት ሃላፊና ምክትሉን ጨምሮ በድምሩ ቢያንስ 6 የሚሆኑ ቋሚ አመራርና ሙያተኞች ይኖሩታል። የኮሚሽኑ ጽ/ቤት ሃላፊ በቢሮ ሃላፊ ደረጃና ምክትል ጽ/ቤት ሃላፊው በም/ቢሮ ሃላፊ ደረጃ ተመድበው የሚሰሩ ናቸዉ።

በዞን እና ለክልል ተጠሪ በሆኑ ከተሞች ደረጃ በአማተርነት ከ 9-11 አመራሮችና በቋሚነት ደግሞ አንድ የጽ/ቤት ሀላፊ በመምሪያ ሀላፊነት እና አንድ ም/ጽ/ቤት ኃላፊ በም/መምሪያ ሃላፊ ደረጃ ተመድበው እንደሚሰሩ የኮሚሽኑ መዋቅር ያዛል። በዚሁ መሰረት ክልላችን ከሁሉም በተሻለ ሁኔታ በሁሉም ዞኖች እና ለክልል ተጠሪ በሆኑ ከተሞች ሁለት ሁለት የኮሚሽን አመራሮችን በቋሚነት መድበው ስራውን እየሰሩ ይገኛሉ። በየዞኑ እና ለክልል ተጠሪ በሆኑ ከተሞች በአማተር አመራርነት ደረጃ 9 በኮንፈረንስና በዞን ፓርቲ ስራ አመራር ተመርጠው እየሰሩ ይገኛሉ። በወረዳ ደረጃ ከ 7-9 አመራሮች በአማተርነት እና አንድ የጽ/ቤት ሃላፊ በቋሚነት ተመድቦ ኮሚሽኑን እንዲመሩ የሰው ሀይል መዋቅሩ ያዛል። በዚህ መሰረት በክልላችን በሁሉም ወረዳዎቻቸዉ አንድ አንድ ቋሚ የኮሚሽን አመራር ተመድበው እየሰሩ ይገኛሉ።

4.2 ኮሚሽኑን የተመለከቱ ዋና ዋና ጉድለቶች

የኮሚሽኑን አመራርና አባል ራሱ ኮሚሽኑን በአመለካከት አሳንሶ የመመልከትና ኮሚሽኑ በትግል ጠንካራ የፓርቲ ተቋም ሆኖ እንዲወጣና ለፓርቲዉ ጉልህ ሚና ይጫወታል ብሎ እንዲጠናከር ቅድሚያ ሰቶ ከመስራት ይልቅ የፓርቲ አስፈጻሚ አካል የሚሰጠዉን ተልእኮ ብቻ ይዞ ለመፈጸም ይታክት ነበር። ብዙ የኮሚሽን ሃይል የፓርቲ አስፈፃሚ አካል በአብዛኛዉ የፓርቲ ቁጥጥርን ስለማይፈለግ የኮሚሽኑን ስራ ብንሰራም የሚቀበለን የለም በሚል አስቀድሞ በአመለካከቱ ይወድቃል። በተመደበበት ነባራዊና ከባቢያዊ ሁኔታ ተንቀሳቅሶ የኮሚሽኑን መዋቅር አደራጀቶ ከማሰመራት ይልቅ ብቻየን ነኝ፣ አልችልም በሚል ምክንያት ተልእኮዉን አይወጣም። በተለይ የኮሚሽኑ አማተር አመራር በትርፍ ጊዜው መስራት ቀርቶ ሌላ መደበኛ ስራ ለመስራት መስክ ሲንቀሳቀስ እንኳ እግረ መንገዱንም ቢሆን የኮሚሽኑን ተልዕኮ ለመፈጸም ዝግጁ አይሆንም። አንዳንዶቹ ደግሞ የተሰየሙበትን የኮሚሽን ስራ ሊሰሩ ቀርቶ መደበኛ የኮሚሽን ስብሰባዎችን ለመሳተፍ እንኳ ሰበቦችን የሚደረድሩ አድርባይ አመራሮች ናቸዉ።

ኮሚሽኑ ለስራ የሚያስፈልገውን በጀትና የስራ መገልገያ ሀብት ማግኘት እንዳለበትና የፓርቲ ጽ/ቤቶችም ይህን ማድረግ እንዳለባቸው ከማዕከል የብልጽግና ፓርቲ ዋና ጽ/ቤትና ከኮሚሽኑ ጽ/ቤት ለክልሎች ሰርኩላር ወርዶ እያለ በትግል ችግሮች እንዲቀረፉ በማድረግ የራሳቸውን መብት እንኳ ማስከበር ያልቻሉ አመራሮች ብዙ ናቸዉ። ኮሚሽኑ የጠቅላላ አባላት መብትና ጥቅሞች እንዲከበሩ ነጻና ገለልተኛ ሆኖ የሚታገል የፓርቲው ተቋም ነው። ሆኖም አንዳንዶቹ የአባላትና የአመራሮችን ችግሮች በትግል እንዲታረሙ ሊያደርጉ ይቅርና የራሳቸው የኮሚሽን አመራሮችን አስፈጻሚው አካል ሲበድላቸዉ፣ ጣልቃ እየገባ እንደፈለገ ከኃላፊነት ሲያነሳና ሌሎች የኮሚሽኑ ስራ የጣሉ የኮሚሽን አመራሮችን ኮሚሽኑ ሳያውቅ ሌላ ሹመት ሲሰጣቸዉ ሰምተዉ እንዳልሰሙ፣ አይተው እንዳላዩ ጉዳዩን የጎሪጥ የሚያልፉና በሹክሹክታ የሚነጋገሩና በአባላት ዘንድም “የአህያ ባል ከጅብ አያስጥል” የሚባሉ የኮሚሽን አካላትም በርካታ ናቸዉ።

5.የአባላት የቅሬታና አቤቱታ አቀራረብና አፈታት ሁኔታ

በፓርቲያችን በህገ-ደንብ አንቀጽ 23 ን/አንቀጽ 6 ተራ ቁርር “ረ” እና “ሰ” ለኮሚሽኑ ከተሰጡት ተልዕኮዎች ውስጥ አንዱ የአባላት መብቶች መከበራቸውን መከታተልና መቆጣጠር እንዲሁም ከአባላት የሚቀርቡ አቤቱታዎችን ይቀበላል፣ ይመረምራል፣ የእርምት የውሳኔ ሀሳቡን ለስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ያቀርባል ይላል። ባለፉት ሶስት አመታት ውስጥ በየደረጃው የሚገኙ **2274** አባላት ቅሬታና አቤቱታቸዉን ለኮሚሽኑ አካላት ያቀረቡ ሲሆኑ ከነዚህ ውስጥ ምላሽ ያገኙት **2216** (97%) ናቸው። በየደረጃው ምላሽ ከተሰጣቸው **2216** ቅሬታዎች ውስጥ ቅሬታቸው ትክክል ነው በሚል ውሳኔ ያገኙት **1221 /55%/** ያህሉ ናቸው። ሌሎች **995 (45%)** አባላት ያቀረቡት ቅሬታና አቤቱታ ተገቢ አይደለም በሚል የተወሰነባቸዉ ዉሳኔ እንዲጸና ተደርጎ ምላሽ ተሰጥቷቸዋል። ይህ ማለት ከቀረቡት ቅሬታዎች መካከል **55%** የሚሆነው ፓርቲው ከአሰራርና ከመርህ ወጥቶ በአባላት ላይ የወሰነው ተገቢነት የሌለው ውሳኔ ነው። ይህ የሚያሳየው ፓርቲው ወደ ፀረ ዲሞክራሲ አካሄድ እየሄደ መሆኑ አንዱ ማሳያ ስለሆነ ቆም ብሎ ሊያስብ ይገባል።

ለአመራርና አባላት ቅሬታና አቤቱታ ምክንያት የሆኑ ጉዳዮችን መመልከት በቀጣይ ፓርቲው በዚህ ረገድ ችግሮችን በእውቀት ላይ ተመስርቶ ለማረምና ለማስተካከል ያስችለዋል። ከለውጡ በፊት በአባላትና አመራር ስምሪት ዙርያ በርካታ የድርጅት ህግ ጥሰቶችና ውሳኔዎች የቅሬታና አቤቱታ ምክንያቶች ነበሩ። በአሁኑ ጊዜም በአባላትና አመራሮች ለቀረቡት ቅሬታና አቤቱዎች ምክንያት ከሆኑ ጉዳዮች መካከል በአብዛኛው አመራሩ ከያዘው ኃላፊነት መነሳት ወይም ከደረጃ ዝቅ ማለት ጋር የተያያዙ ጉዳዮች ናቸው። በዚህ ማዕቀፍ ውስጥ ሆነን ችግሩን ስናይ “በነበረን አመለካከትና የስራ አፈጻጸም ሳንገመገም፣ ተገምግመንም ቢሆን በስራችን ውጤታማና ደረጃችን ከፍተኛ ሆኖ እያለ፣ አመራሮቻችን በመድረክ ስለተቸንና ስለተከራከርን ብቻ፣ ብቃት ሳያንሰን በስልጣን ላይ ረጅም አመት ቆይታችኋልና ይበቃችኋል ተብለን፣ መሰረት በሌለዉ ጥርጣሬና አሉባልታ ምክንያት ተፈርጀን፣ የእነ እገሌ ኔትወርክ አባል ስላልሆን ወዘተ ከያዝነው የኃላፊነት ቦታ ያለምክንያት ዝቅ ተደረግን ወይም ተነሳን” የሚሉ ቅሬታና አቤቱታዎች በስፋት ይቀርቡ ነበር።

6. የሀብትና ንብረት አያያዝና አስተዳደርን በተመለከተ

6.1. የኦዲትና የገቢ ስራን የተመለከቱ ጉዳዮች

በብልጽግና ፓርቲ መተዳደሪያ ደንብ አንቀጽ 23 ንኡስ አንቀጽ **6** ተራ ቁጥር "ሸ" ላይ እንደተገለጸው የፓርቲው ገንዘብ ንብረትና ሰነዶች በአግባቡ መጠበቃቸውን ቁጥጥር ያደርጋል፤ የፓርቲው አባላት መዋጮ በወቅቱ በትክክል መሰብሰቡን ይቆጣጠራል፤ በሚል ለቁጥጥርና ኢንስፔክሽን ኮሚሽኑ ሀላፊነት ሰጥቷል። ከዚህ አንጻር የኦዲት ሪፖርቱ ለኮሚሽኑ ባይሰጠውም ይነስም ይብዛም በክልላችን ሁሉንም ባይሆን የተወሰኑ አመታትን ኦዲት ለማስደረግ ተሞክሯል ። ከዞኖች በተላከልን የውስጥ ኦዲት ሪፖርት መሰረት በዚህ ሶስት አመት በአጠቃላይ 163 ወረዳዎች ኦዲት አስደርገዋል። ኦዲት ከተደረጉት ወረዳዎች ውስጥ በጉድለት የተመዘገበ ገንዘብ **969,109.13** ብር ያህል ነዉ። ከዚህ ጉድለት ውስጥም ለፓርቲው ተመላሽ የተደረገው የገንዘብ መጠን **627,340.98** ብር ብቻ ነው። ቀሪው መሰብሰብ ያለበት **341,768.15** የፓርቲው ብር እስካሁን ድረስ በተለያዩ ምክንያቶ ተመላሽ አልሆነም ወይም እንደባከነ ይገኛል። በተለይ በምስራቅ ጎጃም እና ደቡብ ወሎ ዞኖች በርካታ ገንዘብ የባከነባቸው በመሆኑ ከፓርቲው ጋር በመነጋገር በቶሎና በትኩረት ሊታረም ይገባዋል። ሌሎች ዞኖችም በተሟላ መንገድ የኦዲት ሪፖረት ያላኩ በመኖራቸው እንጅ ጉድለቱ ከዚህ በላይ ሊሆን እንደሚችል ይታመናል። እስካሁን ኦዲት ያላስደረጉ ወረዳዎች በመኖራቸው ፈጥነው የኦዲት ስራ ውስጥ እንዲገቡ ኮሚሽኑ አጥብቆ ክትትል የሚያደርግበት ይሆናል።

6.2. የገቢ አሰባበሰብና የውጭ አጠቃቀም ስራዎችን በተመለከተ

የብልጽግና ፓርቲ መተዳደሪያ ደንብ አንቀጽ 34 የፓርቲው የፋይናንስ ምንጮች ከአባላት እና ከደጋፊዎቹ ናቸዉ ይላል። ሆኖም ከደጋፊዎቻችን የሚገኝን የሀብት ድጋፎች መጠቀም ተገቢም ትክክልም ቢሆንም "የቆጡን አወርድ ብላ የብብትዋን ጣለች" እንዳይሆን አስተማማኝና ቀጣይነት ያለውን የፓርቲ የሀብት ምንጭን ማጠናከር ቅድሚያ ሊሰጠዉ ይገባል። በዚህም በዋነኛነት የአባላችን ቁጥርና ጥራት ማስፋት፣ የአባላትን መብት ማስከበር፣ የገለልተኝነት ስሜት እንዳይሰማዉ በሁሉም የፓርቲ ጉዳዮች ዙሪያ አባሉን ማሳተፍና የፓርቲ የህግ የበላይነትን በማስከበር አባላት የፓርቲ ግዴታቸውን በደስታ እንዲወጡ ማድረግ ይገባል። በብዙ አካባቢዎች ያለው አባል በቅጡ የማይታወቅበት የፓርቲ ክፍያ የማይከፍልበትና በአንዳንድ አካባቢዎችም የአባልነት ክፍያ የሚከፍሉ አባላት መክፈል የሚገባቸዉን ገንዘብ በአሰራሩ ወይም በኖሩሙ መሰረት የማይከፍሉበት ሁኔታም ይታያል።

በህ/ተሰቡ ዘንድ ለፓርቲ ስራ ተብሎ በድጋፍ መልክ የሚሰበሰበው ገንዘብ በርካታ ሲሆን የእቅድና አሰባሰብ መጠናቸው ቢለያይም ሁሉም ዞኖች በዚህ ስራ ላይ ተሳትፈዋል። በዚህም ከ 10 ሽዎች ጀምሮ እስከ ሚሊየኖች ብር ድረስ አቅደው የቻሉትን ያህል ሰብስበዋል። በዚህም ለፓርቲው ድጋፍ ለመስጠት ፍቃደኛ የነበሩ የህ/ተሰብ ክፍሎች ከትንሽ እስከ ትልቅ በደስታ ድጋፋቸውን ለግሰዋል። የተሻለ አቅደው የተሻለ የሰበሰቡ ያሉትን ያክል ትንሽ ከማቀድ ጀምሮ ያቀዱትን ትንሹን እቅድ እንኳን ያልፈጸሙ ዞኖች አሉ። በሂደቱ የነበረዉ ጠንካራ ጎን እንደተጠበቀ ሆኖ በገቢ አሰባሰቡ ወቅት ለተቀበሉት ገንዘብ ደረሰኝ የማይሰጡ ነበሩ፣ የገቢ አሰባሰቡም ወጥ በሆነ እቅድና አመራር ያልተመራ የሚመስልባቸዉ አካባቢዎቹም ነበሩ። የበላይ አካል ድጋፍ የጠየቃቸውን የህ/ሰብ ክፍሎች የበታች አካል ሄዶ የሚጠይቅበት፣ ይህ ብቻም ሳይሆን አንዳንዶቹ አካላት የተጣለባቸውን ኮታ ለማሟላት ሲሉ ድጋፍ ሰጭዎችን የመጫንና የማስጨነቅ ሁኔታም ይታይባቸዉ ነበር። ስራው ምን ያህል ገቢ ተሰበሰበ በሚል

እንጂ ስለሂደቱና ዲሞክራሲያዊነቱ የማይገመገምበት፣ የገቢ አሰባሰቡ ስራ ሲጠናቀቅም በቅጡ ተገምግሞና አዲት ተደርጎ የገባና የወጣው የማይታወቅበት የነበረ ሲሆን ፓርቲዉ ቀጣይ የሚፈትሸዉ መሆን አለበት እንላለን።

6.3 የፓርቲ ንብረት አያያዝና አጠቃቀምን በተመለከተ

ፓርቲያችን የራሱ ሰባዊና ቁሳዊ ሀብቶች አሉት። የአባላትንና የአመራሩን መረጃና ፕሮፋይል በብዙ አካባቢዎች በዘመናዊ መንገድ በዳታ ቤዝ እየገባ ይገኛል። የአባላትን መረጃ ወደ ዳታ ቤዝ የማስገባቱ ስራ ቀደም ብሎ የተጀመረና መልካም ቢሆንም ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በተደረገው ልዩ ርብርብ አፈጻጸሙ ከ 97 በመቶ በላይ ማድረስ ተችሏል። ለቀጣይ ቢሆን እነደዚህ አይነት ተግባራት የፖለቲካ አመራሩ ስራዉን በትኩረት ይዞና ባለቤት መድቦ በቶሎ ማጠናቀቅና በየጊዜዉም ወቅታዊ/Update እያስደረገ መሄድ አለበት። ፓርቲ ጽ/ቤቱን 3 ጊዜ በደብዳቤ የፓርቲውን ሰባዊ፤ቁሳዊና የገንዘብ ሀብትን አሳውቁን ተብሎ ቢጠየቅም መልስ ማግኘት አልተቻለም። ያም ሆነ ይህ ከሰብአዊ ሃብት አንጻር ቁሳዊ ሀብቶችን በሚመለከት የፓርቲው ቁሳዊ ሀብቶች በዋነኛነት ተሽከርካሪዎች፣ የፓርቲው ጽ/ቤቶችና መገልገያ ቁሳቁሶች መሆናቸው ይታወቃል። በተለያዩ የስራ ስምሪቶች ወቅት ለመረዳት እንደተቻለው በብዙ አካባቢዎች የፓርቲ የገንዘብ ብክነትና ሌብነት፣ የንብረት አያያዝና አጠቃቀም፣ ሃብት ስርጭትና የፍትሃዊነት ችግሮች በተወሰነ ደረጃ ይታያሉ። ከምንጊዜውም በተሻለ ሁኔታ የብልጽግና ፓርቲ ጽ/ቤት ለዞኖችንና ለከተማ አስተዳደሮች በተሽከርካሪ በኩል የሚስተዋሉባቸውን ችግሮች ለመቅረፍ ያደረገው ጥረት አድናቆት የሚቸረዉ ቢሆንም በአንድ በኩል ግዴታቸዉን ላልተወጡ ዞኖች ድጋፍ ማድረግ ያልነበረበት ሲሆን በሌላ በኩል ምንም መንቀሳቀሻ የሌላቸዉን የኮሚሽን ጽ/ቤቶች ታሳቢ ቢያደርግ ጥሩ ነበር።

ሌላው ከፓርቲ አላማ፣ መተዳደሪያ ደንብና አሰራር ዉጭ ወይም የፓርቲዉ ስራ አሰፈጻሚ ኮሚቴ ሳይወስን በክልል ፓርቲ ጽ/ቤት ዉሳኔ ብቻ የፓርቲዉን ብር ለግለሰቦችና ለተለያዩ አካላት በብድርና በድጋፍ መልኩ ተሰጥቷል። የፓርቲዉን ገንዘብ ግልጽነት፣ ፍትሃዊነትና ተጠያቂነትን በማያሰፍን ሁኔታ በተለይ በብድር ስም በጣም በተራዘመ የክፍያ አመታት መዉሰዱ ስህተት ብቻ ሳይሆን ተጠያቂም ያደርጋል። ያለ ጠንካራ አሰራርና ዉል፣ ያለ ወለድ፣ ያለ ጠንካራ የብድር ማስያዥያ (Colateral) በደሞዝና በተራ የሰዉ ዋስትና ብቻ እንደ ማስያዥያ እየተደረገ ብድር ተሰጥቷል። ይህ ሁኔታ በጣም ትክክል ያልሆነና በፍጥነት የእርምት እርምጃ ሊወሰድበት የሚገባ ጉዳይ ነዉ።

ለአመታት ሲንተቱ የነበረው የምስራቅ ጎጃም ዞን የቢሮ ግንባታ የገንዘቡን መጠን ማወቅ ባንችልም እንዲጠናቀቅ በጀት የተመደበ መሆኑ የሚመሰገን ሲሆን እስካሁን ለፍጻሜ አልደረሰም። በተመሳሳይ የማእከላዊ ጎንደር ዞን ቢሮ አገልግሎት እየሰጠ ቢሆንም ያላለቁ ስራዎች እንዳሉ መታዘብ ችለናል።

ሌላው መታየት ያለበት አስገዳጅ የፓርቲ ተግባራት ሲኖሩ የፓርቲን ተሽከርካር መጠቀም አሳማኝና ተገቢ ቢሆንም በክልልም ሆነ በዞን ደረጃ የሚገኙ የተወሰኑ የፓርቲ ጽ/ቤት አመራሮች ለየት ያለ የፓርቲ ተልእኮ በሌለበትም ወቅት በመንግስት በኩል የተመደበላቸው ተሽከርካሪና ነዳጅ እያላቸው በተጨማሪነት የፓርቲውን ተሽከርካሪ እያፈራረቁ ሲጠቀሙ ይስተዋላል። በሌላ በኩል ከዚህ በፊት ለፓርቲው አገልግሎት ይሰጡ የነበሩና በአሁኑ ስአት ጥቅም የማይሰጡ ተሽከርካሪዎች በቆይታ፣ በፀሃይና

ዝናብ ብዛት ለከፋ ብልሽት ከመዳረጋቸው በፊት በጨረታ የሚሸጡበት ሁኔታ እንዲመቻች ቢጠቆምም እስካሁን ተፈጻሚ አልተደረገም።

7. የተለዩ ምክረ-ሃሳቦች/ማጠቃለያ

7.1. የፓርቲ አስፈጻሚ አካላትን የተመለከቱ ምክረ-ሃሳቦች

1. አንድ የፖለቲካ ፓርቲ ጠንካራ ሆኖ ሊቀጥል የሚችለው ራሱ ያወጣውን ህግና አሰራር በጠንካራ ዲሲፒልን ሲፈፅምና ሲያስፈፅም ብቻ ነው። መሆን ያለበት ይህ ሆኖ ሳለ በደረጃዉ የሚገኝ ቱባ ቱባ አመራር ሳይቀር የፓርቲዉን መተዳደሪያ ደንብ፣ አሰራርና መርህ እየጣሰ በአባላትና አመራሮች ላይ የተለያዩ ዉሳኔዎችን ሲያሳልፍ ቆይቷ። ይህ ሁኔታ በበርካታ አባላትና አመራሮች ዘንድ በፓርቲው ላይ ቅሬታና የእምነት ማጣት ስሜት እንዲፈጠር በማድረግ የፓርቲውን መሠረት እየተፈታተነው ይገኛል። ስለዚህ ፓርቲው እራሱ ያወጣውን ደንብና አሠራር በማወቅም ሆነ ባማወቅ እየጣሱ የውስጠ ፓርቲ ዲሞክራሲን በሚያቀጭጩ አመራሩች ላይ የማያዳግም የዲስፒሊን ቅጣት መቅጣትና የፓርቲ የህግ የበላይነት እንዲከበር መደረግ አለበት።

2. የፓርቲ ዲስፕሊን የሚከበረውና ብልሹ አሰራርን መከላከል የሚቻለው፣ የፓርቲ የህግ የበላይነት ሊከበር የሚችለው ብሎም ፓርቲውን ከጠላትና ከሰርጉ ገቦች መጠበቅ የሚቻለው አካላት/ተቋማት በሥራቸው ሲገመገሙና አመራርና አባላቱ ሂስና-ገለሂስ ሲያካሂዱ ነው። ይህ መርህ ለአንድ ጠንካራ ፓርቲ መኖር በጣም መሠረታዊ ጉዳይ ሆኖ ሳለ በአሁኑ ሰአት ግን በአንዳንድ አካባቢዎች ላይሰሙት/ለፕሮሲጀር ካልሆነ በቀር ፓርቲያችን በውስጡ ያጋጠመውን በርካታ ብልሽትና የአሰራር ጥሰት ችግሮችን በፍጥነት ሊያርም የሚችል ግምገማና ሂስ-ግለሂስ የለም። “ሊበሏት ያሰቧትን አሞራ.... ይሏታል” እንዲሉ አንዳንድ የፓርቲዉ አመራሮችም ግምገማና ሂስና ግለ-ሂስ የአብዮታዊ ዴሞክራሲ መሳሪያ ነዉ በሚል የሚነቅፋቸዉን ሰዉ ሊያሸማቅቁት ይሞክራሉ። በመሆኑም እዉነተኛ የስራ ግምገማ እና ሂስና ግለሂስ በተቀመጠለት ጊዜ፣ አሰራርና መርህ መሰረት ሳይዛነፍ እንዲካሄድ በማድረግ ፓርቲው እራሱን በራሱ በየጊዜው እያረመና እያጠራ፣ የሚታረሙትን እያረመና ተመክረዉና ተዘክረዉ የማይለወጡትን ድግሞ እንደ አግባቡ ቦታ ቦታቸዉን እያስያዘ የብልጽግናን ጉዞ ማስቀጠል ይገባል።

3. ፓርቲያችን የፖለቲካና የፓርቲ ሥራዎችን የሚከውነው በዋንኛነት ከአባላችን በሚገኝ ወርሃዊ መዋጮና ከደጋፊዎቻችን በሚገኝ ድጋፍ ነው። ከህብረተሰቡ በድጋፍ መልክ የሚገኘዉ ገቢ ችግር አለበት ባይባልም ከገቢ አሰባሰቡ፣ ከክትትልና ቁጥጥር አግባቡ አንጻር ግን በርካታ ችግሮች በተለያዩ አካባቢዎች መስተዋሉን ከላይ ተመልክተናል። በመሆኑም ይህ ሁኔታ አደገኛና ለከፋ ብልሽትና የሃብት ብክነት የሚዳርግ፣ የፓርቲዉንም ሆነ የመንግስትን ታማኝነት በአባላትም ሆነ በህዝቡ ዘንድ የሚያቀጭጭ ድርጊት ስለሆነ በተሎ መታረም አለበት። ስለሆነም ፓርቲው የባለፉትን የገቢ ማሰባሰቢያ ጊዜዎች በልዩ ሁኔታ ኦዲት አድርጎ የነበረዉን ተጨባጭ ሁኔታ ማወቅና ለቀጣይ ደግሞ የብልሹ አሰራር ቀዳዳዎችን በሚደፍን መልኩ ተገቢ የአሰራር ማስተካከያ ማድረግ ይኖርበታል።

7.2. ኮሚሽኑን በሚመለከት የቀረበ ምክረ-ሃሳብ

1. አንድ በፓርቲ የዉስጥ ጉዳይ ዙሪያ ክትትልና ቁጥጥር የሚያደርግ ተቋም ከሚቆጣጠረው አካል ጋር ያለው የሰው ሀይል፣ የማስፈጸምና የመደመጥ አቅሙም ሆነ የተቋሙ አደረጃጀት ከማንም ተጽኖ ሳይደርስበት በነጻነትና በልበ ሙሉነት መንቀሳቀስ አለበት። በአሁኑ ጊዜ ፓርቲያችን እየገዘፈ፣ ተግባርና ተልእኮዎቹም እያደር እያደጉና እየተወሳሰቡ፣ የሚመራዉ የሰዉ ሃይልም እጅግ እየሰፋ፣ መዋቅራዊ

ቅርጹም እየተለጠጠ፣ ሰርጎ ገቦችም ሆኑ ዉጫዊና ዉስጣዊ ባላንጣዎቹ በዚያዉ ልክ እያደጉ በመምጣት ላይ ይገኛሉ። ስለሆነም ኮሚሽኑ አሁን በመተዳደሪያ-ደንብ ከተሰጠዉ የቁጥጥርና ክትትል ተልዕኮ በጣም ላቅ ያለ፣ የፓርቲዉን የፖለቲካ ሽክም የሚያቃልል፣ በሰዉ ሃይል፣ በበጀትም ሆነ በቁሳቁስ ከልመናና ደጅ ከመጥናት የወጣ የአመራር ስምሪትና ደረጃዉም/Status ከአሰፈጻሚው አካል ከፍ ያለ አልያም በአቻ ደረጃ እንዲሆን መደረግ ይኖርበታል።

2. ለአንድ የፖለቲካ አላማ መሳካት የቆሙ ነገር ግን በፓርቲ መተዳደሪያ-ደንብ ተለይቶ በተሰጣቸዉ ተግባርና ሃላፊነት የሚንቀሳቀሱ የአንድ ፓርቲ ሁለት አካላት በግልጽ በተቀመጠ የመገናኛ ጊዜ እየተገናኙ በፓርቲ ጉዳዮች ዙሪያ እየተነጋገሩ ጥሩዉ ነገር እንዲቀጥል ጉድለቶች ደግሞ ሳይዉሉ ሳያድሩ እንዲታረሙ መስራት ይገባቸዋል። በመሆኑም በቀጣይ ፓርቲዉ በጥንካሬ እንዲዘልቅና በፓርቲዉ ዉስጥ የሚታዩ ችግሮችም የከፋ ጉዳት ከማድረሳቸዉ በፊት እንዲታረሙ ለማድረግ የጋራ የግንኙነት ጊዜ ተቀምጦ ጉባኤ ሲደርስ ለሪፖርት ብቻ ሳይሆን በየጊዜዉ በጋራ እየተገናኙ መነጋገር ያስፈልጋል። በመሆኑም በፓርቲዉ በህግ/አሰራር ዉስጥ የጋራ የግንኙነት ጊዜ ተደንግጎ ሊቀመጥና ሊተገበር ይገባል እንላለን።

3. አንዳንድ የፓርቲዉ አመራሮች ኮሚሽኑ በመተዳደሪያ-ደንቡ በተሰጠው ተልዕኮ መሰረት የሰራዉን ስራ መነሻ አድርጎ የተፈጠሩት የፓርቲ የህግ ጥሰቶች እንዲስተካከሉና ፓርቲዉን የሚጠቅሙ ምክረ-ሃሳብ ሲያቀርብ አንቀበልም በማለት የፓርቲዉን የቁጥጥርና ክትትል ስምሪት ሲያደናቅፉ ይታያል። በመሆኑም ኮሚሽኑ የፓርቲዉን መተዳደሪያ-ደንብ መሰረት አድርጎ የሚያወጣዉን የኮሚሽን መመሪያና አሰራር በፓርቲው አስፈጻሚ አካላት ዘንድ ሙሉ ሙሉ ተፈፃሚነት እንዲኖራቸው የሚያሰገድድ የፓርቲ ህግ ከተጠያቂነት አሰራር ጋር መቀመጥ አለበት።

4. ከኮሚሽኑ ተልዕኮ ጋር በማይጋጭ መልኩ ሁሉንም የፓርቲ አባላትና አካላት የሚመለከቱ ተግባርና ሃላፊነቶች ማለትም በየደረጃዉ የሚካሔዱ የጉባኤና የኮንፈረንስ ዝግጅቶች ሲኖሩ፣ የፓርቲ መተዳደሪ ደንብና ፕሮግራም ሲሻሻል፣ የፓርቲ በዓላት ወዘተ ሲኖሩ ኮሚሽኑ በደረጃዉ በኮሚቴ ዉስጥ መሳተፍ ይገባዋል። የሁሉም አባል ተግባራት በሆኑ ጉዳዮች ማለትም በምርጫ ስምሪት፣ በሰላምና ፀጥታ ማስከበር ወዘተ ስራዎች ላይ የኮሚሽኑ አባልና አመራር እንደ ተቋም ተልዕኮ ተሰቷቸዉ መሰማራት አለባቸው። ከዚህም ሌላ ለሌሎች አባላትና አመራሮች እንደሚደረገዉ ሁሉ የፓርቲዉ የስልጠና ትምህርት፣ የግንዛቤ ማስጨበጫ መድረኮች እና አጠቃላይ የአመራርና አባላት መድረኮች ሲኖሩ ኮሚሽኑ የተሳትፎ እድሎች እንዲያገኝ መደረግ አለበት። የፓርቲ ሹመትና ምደባዎች ሲኖሩ የኮሚሽኑ አመራሮችና አባላት እንደ ተቋም/አካል ሳይዘነጉ እኩል የሚታዩበት ሁኔታ እንዲሁም የፓርቲ መተዳደሪያ ደንብ፣ አላማና ፕሮግራምን እና የአባላት ዲስፕሊንን ከተልእኮቻቸዉ ጋር እያስተሳሰሩ ማስተማርና ማስረጽ ለፓርቲዉ በጣም ይጠቅመዋል። በመሆኑም ከላይ በተዘረዘሩት ጉዳዮች ዙሪያ የኮሚሽኑ በየደረጃዉ የሚሳተፉበትና እድል የሚያገኝበት የፓርቲ የአሰራር ሥርዓት መፈጠር አለበት።

7.3. ማጠቃለያ

በፓርቲዉ ዉስጥ በርካታ የዉስጠ ፓርቲ ዲሞክራሲ ችግሮችና የህግ የበላይነትን የማስከበር ችግር ያጋጠመን ከመሆኑም ሌላ ፓርቲዉም ሆነ አባላቶቹ የሚያገኙትን መልካምይ ይሁን ክፉ አጋጣሚዎች በሚገባ በመጠቀም ለፓርቲዉ ጥንካሬና ግንባታ ስራ

አላዋሉትም። የፓርቲዉን አላማና አሰራሮች በእምነትና በጽናት ይዞ በመንቀሳቀስ በፓርቲዉ ዉስጥ የተግባርና የሃሳብ አንድነት እንዲፈጠር አልተደረጉም።

እንደ ፓርቲ በአመራሩና በአባላት ውስጥ እርስ በርስ መጠራጠርና የግንኙነት መሻከር፣ በየማህበራዊ ሚዲያዉ በስዉርም ይሁን በግልጽ ጎራና ዘር ለይቶ መወራረፍና መነታረክ፣ የሰርጎ ገቦች መበራከትና የጎራ መደበላለቅ መኖር፣ ግልጽነትና አሳታፊነት የጎደለው፣ ከመርህና ከአሰራር ዉጭ በትዉዉቅ የሚፈጸም መሳሳብና የሰው ሀይል ስምሪት መኖር፣ የህዝብ አገልጋይነት እየተዳከመ ሌብነትና ብልሹ አሰራር መስፋፋት፣ እርስ በርስ መጠቃቃትና የታገለህን አባልና አመራር ሰበብ ፈልጎ ማሳደድና መጉዳት፣ አመራሩም ሆነ መዋቅሩ በየአካባቢዉ የጸጥታ መደፍረስና የሰዉና የንብረት ዉድመት ችግሮች ሳይፈጠሩ ቀድሞ ሁኔታን እያጠኑ መከላከል አለመቻልና የአላማ የጽናት ማዳከም፣ በየጊዜው በግምገማ እና በሂስና ግለ-ሂስ ዉስጡን እያጠራ ያለመሄድና የመድረክ ፍራቻ መሰፈንና የዉስጥ ዴሞክራሲ መቀጨጭ ብሎም ግልፅነትና ተጠያቂነት የጎደለው ለብክነትና ሌብነት የተጋለጠ የሃብት አስተዳደርና የመሳሰሉት ውስጣዊ ድክመቶችና ችግሮች አሉበት። የዚህ ችግር መሰረታዊ ምክንያት ደግሞ ሁሉንም አመራር የሚመለከት ቢሆንም በዋነኛነት ግን በየደረጃዉ በሙሉ ሰአት ስራ ፓርቲዉን እየመራ ያለዉ የፓርቲ ጽ/ቤት ችግር መሆኑ እንኳን እኛ ፖለቲካን በቅጡ መተንተን የማይችለዉ ተራ ሰዉ እንኳ በቀላሉ የሚረዳዉና በምንም አይነት ቀለም ቀባብተን ልንሸፍነዉ የማንችለዉ ነጭ እዉነት ነዉ።

በመሆኑም ፓርቲዉም ሆነ መንግስት እያስመዘገቡ ያሉት በርካታ ስኬቶችና ዉጤቶች ህዝብንም ሆነ ሃገርን የታደጉና የጠቀሙ ቢሆንም በአሁኑ ሰአት በፓርቲዉ ዉስጥ እየተስተዋሉ ያሉ ድክመቶቹንና ተግዳሮቶችን መዋቅሩን፣ አባልና አመራሩን ከማጥራት በመጀመር ስርነቀል በሆነ መንገድ ፈትቶ የጀመረዉን የብልጽግና ጉዞ ከግብ በማድረስ የሃገርና የህዝብን መልከ ብዙ መሰረታዊ ችግሮች መፍታት የሚችል ቁመና ላይ በአጭር ጊዜ ዉስጥ ሊይዝ ይገባዋል።

የፓርቲዉ ቁጥጥርና ኢንስፔክሽን ኮሚሽን በመተዳደሪያ-ደንቡ የተሰጠውን ተግባርና ኃላፊነት ለመፈጸም ከነዉስንነቱም ቢሆን የበኩሉን እንቅስቃሴ ሲያደረግ ቆይቷል። ኮሚሽኑ በአለፉት ዓመታት የፓርቲው መተዳደሪያ ደንብን መሰረት በማድረግ ከአባላትና አመራሮች ሲቀርብለት የነበሩትን ቅሬታዎችና አቤቱታዎች በማጣራት አግባብነት ያላቸዉን ምልሽ ሲሰጥ ቆይቷል። አመራርና አባላት ያቀርቡዋቸዉ የነበሩ ቅሬታዎችና አቤቱታዎች በአብዛኛዉ እዉነትና ተገቢነት የነበራቸው ነበሩ ማለት ይቻላል።

ከላይ የተገለጹት ጥንካሬዎችና ችግሮች ኮሚሽኑንም የሚመለከቱ ቢሆንም ኮሚሽኑ በራሱ መዋቅራዊና ውስጣዊ ችግሮች ምክንያት ኮሚሽኑን ከማጠናከርም ሆነ ፓርቲዉን ከመደገፍ አንጻር ተገቢዉን ትግል በማድረግ የሚጠበቅበትን ያህል አልተወጣም። በዚህ ረገድ የኮሚሽኑ ብዙ አመራር ሰፊ የአመለካከት መዛነፍ ችግሮች ነበሩበት። በተለይም በአማተርነት የሚሰራዉ አመራር ግልጽ የተጠያቂነት ስርአት ስላላሰፈንን ለኮሚሽኑ ስራና መደበኛ ስብሰባዎች ትኩረት የሚሰጥ አልነበረም። አስፈጻሚዉም ቢሆን ያለዉን ያበጠ የፓርቲ ስልጣን መከታ አድርጎና ኮሚሽኑን ዝቅ አድርጎ በማየት በኮሚሽኑ ስራና የሰዉ ሃይል ስምሪት ላይ ጣልቃ እየገባ አላላዉስ አላንቀሳቅስ ይልም ነበር።

በአጠቃላይ ሲታይ የፓርቲዉ አስፈጻሚ አካላትም ሆኑ ኮሚሽኑ የሚስተዋልባቸዉን መዋቅራዊና የአሰራር ዉስጠ ፓርቲ ችግሮች በልዩ ሁኔታ ገምግመዉና ፈትሸዉ በፍጥነት ማስተካከል ካልቻሉ በቀር ፓርቲዉንና መንግስትን ብሎም ሃገርንና ህዝብን ከባድ ፈተና ዉስጥ የመክተት አቅማቸዉ ሰፊ ነዉ። ኮሚሽኑ በፓርቲዉ መተዳደሪያ ደንብ የተሰጡትን ተግባርና ኃላፊነቶች በእግባቡ እንዲወጣ ከተፈለገ ቀደም ሲል ያቀረባቸውን የግምገማ ሃሳቦችና ምክረ ሃሳቦች በየደረጃው በሚካሄዱት ኮንፈረንሶችና በፓርቲው ጠቅላላ ጉባኤ ላይ በቂ ውይይትና ምክክር ሊደረግባቸዉና የኮሚሽኑ ሁለንተናዊ ተቋማዊ አቅም ተጠናክሮ ለፓርቲዉ ሁነኛ አቅም የሚሆንበት እድል ሊፈጠር ይገባል እንላለን።

የአማራ ብልጽግና ፓርቲ ቁጥጥርና ኢንስፔክሽን ኮሚሽን

የካቲት 2014 ዓ.ም፣ ባህር ዳር